# በዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ጊዜ ፡ የነበረው ፡
# የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ ይዞታ ፡ (፲፱፻፵፬—፲፱፻፶፭)

ከጆርጅ ቸቺኖቪች ።*

በመጀመሪያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስለነበረው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ታሪክ ፡ አንድ ፡ የተለየ ፡ ጽሑፍ ፡ ለማበርከት ፡ ሃሳብ ፡ ነበረኝ ። ይህንንም ፡ ሃሳብ ፡ ከግቡ ፡ ለማድረስ፡ በ፲፯ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ተተርጉሞ ፡ የነበረውን ፡ የነገሥታትና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ (ፍትሐ ፡ ነገሥት) ፡ በምን ፡ ዘዴ ፡ በየቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ይሰጥ ፡ እንደነበረ ፡ ለማስረዳት ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ የሚሠራ ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሊቅ ፡[1] አስፈለገኝ ። ነገር ፡ ግን ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ ለመሥራት ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ ፈቃደኛ ፡ የሆነ ፡ አላገኘሁም ። ስለዚህ ፡ ስለጉዳዩ ፡ የሚያውቁና ፡ ያልረሱ ፡ ሰዎች ፡ በሕይወት ፡ ባሉበትና ፡ የመንግሥትም ፡ ሆኑ ፡ ሌሎች ፡ መዛግቦች ፡ በሚገኙበት ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የኔን ፡ ድርሻ ፡ ለማበርከት ፡ ወሰንኩ ።[2]

፲፱፻፵፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕጎች ፡ አጠናቅቆ ፡ በመጽሐፍ ፡ መልክ ፡ ለማውጣት ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ በማድረግ ፡ ረቂቁን ፡ የማዘጋጀቱን ፡ ኃላፊነት ፡ ከአውሮፓ ፡ አህጉር ፡ ለመጡ ፡ ለፈረንሣይ ፡ ሊቃውንት ፡ ሰጡ ።[3] ምንም ፡ እንኳን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፤ የንግድና ፡ የፍትሐብሔር ፡ ሕጎች ፡ አስተዋጽኦ ፡ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጀምሮ ፤ የወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም፤ የንግዱና ፡ የፍትሐብሔሩ ፡ ሕጎች ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፤ ሕግ ፡ ሆነው ፡ እንዲታወጁ ፡ ቢታቀድም ፡ እነዚህን ፡ ሕጎች ፡ ተረድተው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ ሕጎቹ ፡ ከመውጣታቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ማዘጋጀት ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ። የአዲስ፡ አበባው ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተመርቆ ፡ ተከፍቶ፡

* በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ ፕሮፌሰር ፤ ከ፲፱፻፵፭—፲፱፻፶፪ ፡ የዩኒቨርስቲ ፡ ኮሌጁ ፡ ሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ዲን ።

1. የኢትዮጵያ ፡ ጥናትና ፡ ምርምር ፡ ድርጅት ። ሬጅስተር ፡ ኦፍ ፡ ከረንት ፡ ሪሰርች ፡ (፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡)

2. በዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ዘመን ፡ የነበረው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ከ፲፱፻፵፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ በዚህ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ ከሚወጣው ፡ ከዲኑ ፡ ሪፖርት ፡ ጋር ፡ ተወዳዳሪ ፡ በሆኑ ፡ ዓመታዊ ፡ መጽሔቶች ፡ ተገልጾ ፡ አያውቅም ። የተዘነጋውም ፡ በሌሎች ፡ ምክንያቶች ፡ ጭምር ፡ ነው ። እስከ ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሕግ ፡ ት/ቤቱን ፡ አብዛኞቹን ፡ ሪኮርዶች ፡ የሚይዘው ፡ ዲኑ ፡ ነበር ። በኋላም ፡ ሪኮርዶቹ ፡ ይጠፉ ፡ ጀመር ። በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሕብረት ፡ የተቋቋመው ፡ የኮሌጁ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ለአንዳንድ ፡ ወረቀቶች ፡ መጥፋትና ፡ ለፊተኛው ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ መውደም ፡ ምክንያት ፡ ሆነ ። እንደገና ፡ በ፲፱፻፶፮ ፡ የኮሌጁ ፡ ሪኮርዶች ፡ ወደ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሲዘዋወሩ ፡ ተጨማሪ ፡ ሪኮርዶች ፡ የጠፉ ፡ ይመስላል ። ስለዚህም ፡ በፊተኞቹ ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ሪኮርዶች ፡ ያልተገኙ ፡ አንዳንድ ፡ ጉድለቶች ፡ በቃል ፡ ማስታወስ ፡ ብቻ ፡ እንዲሞሉ ፡ ሆነ ። እንዲሁም ፡ እዚህ ፡ ጸሐፊ ፡ ዘንድ ፡ የነበሩት ፡ ግልባጭ ፡ ሪኮርዶች ፡ በመስከረም ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጸሐፊው ፡ ዘንድ ፡ የነበሩት ፡ ግልባጭ ፡ ሪኮርዶች ፡ በመስከረም ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጸሐፊው ፡ በሌለበት ፡ ወቅት ፡ ከሳጥኑ ፡ ውስጥ ፡ በከፊል ፡ ጠፍተው ፡ ወይም ፡ ተዘበራርቀው ፡ ስለተገኙ ፡ በቃል ፡ በማስታወሻ ፡ ማሟላት ፡ አስፈልጓል ።

3. የአሜሪካን ፡ ሊቃውንት ፡ የተሻሻለውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በማርቀቅ ፡ ረድተዋል ።

ስለነበር ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ለማቋቋም ፡ የትምህርት ፡ መሠረት ፡ ዝግጁ ፡ ሆነ ። የግር ማዊነታቸው ን ፡ ፍላጐት ፡ በመከተል ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ በቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ መሠ ረት ፡ አንዳንድ ፡ የሕግ ፡ ትምህርቶች ፡ ከጥር ፡ ጀምሮ ፡ ለማስተማር ፡ ታቅዶ ፡ ትምህ ርቱ ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጀመረ ። ይህ ፡ "ለሙከራ" ያህል ፡ ተብሎ፡ የተሰጠው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ባስገኘው ፡ ውጤት ፡ መደሰቱን ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ገለጸ ። በመስከረም ፡ ወር ፡ ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የአዲስ ፡ አበባው ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ፡ የአርትስ ፤ የሣይንስ፡ ፋክልቲዎችና ፤ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ በመባል ፡ የሚጠሩ ፡ እያንዳን ዳቸው ፡ በዲን ፡ የሚመሩ ፡ ሦስት ፡ ክፍሎች ፡ እንዳሉት ፡ በገሃድ ፡ ታወቀ ። የአርት ስና ፡ የሣይንስ ፡ ፋክልቲዎች ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ ትምህርት ፡ ሲሰጡ ፤ የሕግ ፡ ት/ቤቱ ፡ ግን ፡ "በሕግ ፡ ሙያ ፡ ተሰማርተው" ለሚሰሩ ፡ ትምህርቱን ፡ ለማሳተፍ፡ በማሰብ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ብቻ ፡ ያስተምር ፡ ነበር ።[4]

ኮሌጁ ፡ በሌሎች ፡ የትምህርት ፡ መስኮች ፡ የሰጠው ፡ ፍሬ ፡ በኮሌጁ ፡ ከተሰጠው፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ጋር ፡ ሲነፃፀር ፡ የሕጉ ፡ ትምህርት ፡ አጀማመሩ ፡ ጥሩ ፡ የተስፋ ፡ ጭላንጭል ፡ ያሳየ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ የኋላው ፡ ታሪኩ ፡ ግን ፡ ያለማቋረጥ ፡ እየተምዘገዘገ ፡ መውደቁ ፡ ነው ። የሕግ ፡ ት/ቤቱ ፡ ታሪካዊ ፡ እርምጃ ፡ በሚከተሉት ፡ እርእሶች ፡ ሊከ ፈል ፡ ይችላል ።

ሀ/ ተስፋ ፡ ያለው ፡ አጀማመር ፤ የመጀመሪያው ፡ መሠረታዊ ፡ የሕግ ፡ ትም ህርት ፡ ኮርስ ፡ (፲፱፻፵፬—፵፯ ዓ ፡ ም ፡) ፤

ለ/ የሕግ ፡ ሙያ ፡ ትምህርት ፡ መሰጠት ፡ መታገዱና ፡ (፲፱፻፵፰ ዓ ፡ ም ፡) "የሕግ ፡ ፋክልቲ" ፡ ችግር ፡ (ከ፲፱፻፵፰—፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ፤

ሐ/ በሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ይሰጥ ፡ የነበረው ፡ ከፍተኛ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ (ከ፲፱፻፵፱—፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ፤

መ/ በሕግ ፡ ት/ቤት ፡ የተሰጠው ፡ ሁለተኛ ፡ መሠረታዊ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፤ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ መዘጋት ፡ (ከ፲፱፻፵፱—፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ፤

ሠ/ ሕግ ፡ "ሜፍ ፡ ሜፉን" ብቻ ፡ በአርትስ ፡ ፋክልቲ ፡ ማስተማር ፡ መጀመሩ ፡ (ከ፲፱፻፵፯—፶፫ ዓ ፡ ም ፡ ) ፤

ረ/ የኮሌጅ ፡ ዘመን ፡ ፍጻሜና ፡ መደበኛ ፡ የሆነው ፡ የሕግ ፡ ሙያ ፡ ትምህርት፡ እንደገና ፡ ማበብ ፡ (፲፱፻፶፮—ዓ ፡ ም ፡) ።

## ሀ/ ተስፋ ፡ ያለው ፡ አጀማመር ፤ የመጀመሪያው ፡ መሠረታዊ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ኮርስ ፡ (፲፱፻፵፬—፵፯)

የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤትን ፡ ዲንም ፡ ሆነ ፡ የኮሌጁን ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ስለትምህርት፡ ቤቱ ፡ የገጠማቸው ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ መሠረታዊ ፡ ችግሮች ፡—

4. "በንግድ ፡ አስተዳደር ፡ በሂሳብ ፡ ሥራና ፡ በሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ሥራዎች" የተሰማሩትን ፡ የማታ ፡ ተማሪዎች ፡ ችሎታ ፡ ለማሻሻል ፡ በማሰብ ፡ በአርትስ ፡ ፋክልቲ ፡ ሥር ፡ ከጥር ፡ ወር ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ ተከፈተ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዩ.ኮ. መጽሔት ፡ ብለን ፡ የምንጠቅሰውን ፡ የ፲፱፻፵፬—፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እና ፡ የ፲፱፻፵፯—፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ መጽሔት ፡ ይመለከቷል ።

፩/ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ለማንና ፡ የትስ ፡ መሰጠት ፡ እንደሚገባው ፤

፪/ ትምህርቱ ፡ በምን ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ እንደሚሰጥ ፤

፫/ የማስተማሩን ፡ ተግባር ፡ ማን ፡ እንደሚያከናውነው ፤

፬/ የትኛው ፡ ሕግ ፡ ለትምህርት ፡ እንደሚቀርብ ፤ የመወሰኑ ፡ ተግባር ፡ ነበር ።

### ፩/ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ለማንና ፡ የትስ ፡ ይሰጥ ?

ከሌሎቹ ፡ ብዙ ፡ የአፍሪቃ ፡ ሀገሮች ፡ ጋር ፡ ስትወዳደር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚችሉ ፡ ምሁራን ፡ አልነበሯትም ። ለዚህም ፡ በከፊል ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ከ፲፱፻፳፰ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ ኢጣሊያ ፡ ካደረገችው ፡ ያልተሟላ ፡ ወረራ ፡ በስተቀር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነፃነቷን ፡ አጥታ ፡ የማታውቅ ፡ ሀገር ፡ በመሆንዋ ፡ በቀሩት ፡ "የእንግሊዝ" ወይም ፡ "የፈረንሣይ" ቅኝ ፡ ግዛት ፡ በነበሩት ፡ የአፍሪቃ ፡ ሀገሮች ፡ እንደተደረገው ፡ ሁሉ ፡ በቅኝ ፡ ገዥዎችም ፡ ሆነ ፡ በጠባቂዎች ፡ ሕግ ፡ የሰለጠኑ ፡ የሕግ ፡ ምሁራን ፡ አለመኖር ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ በሃሳብም ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ የማንም ፡ ጥገኛ ፡ ሳትሆን ፡ ለመኖር ፡ ለነበራት፡ ፍላጐት ፡ በጊዜው ፡ ረቂቃቸው ፡ ወደማለቁ ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ ሕጐቻ ፡ ከተለያዩ ፡ የሕግ ፡ ዘርፎች ፡ የተውጣጡ ፡ እንዲሆኑ ፡ በማቀድ ፡ የማዘጋጀቱን ፡ ሥራ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀገር ፡ የሕግ ፡ ሥልቶች ፡ ባለሙያዎች ፡ ለሆኑ ፡ ሊቃውንት ፡ መስጠቷ ፡ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ። ከዚያም ፡ የተነሳ ፡ ሕግ ፡ ከሚያጠኑት ፡ ኢትዮጵያውያኖች፡ አብዛኞቹ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሄደው ፡ በሌላ ፡ የሕግ ፡ ስልት ፡ ከመሰልጠን ፡ ይልቅ ፡ የሀገራቸውን ፡ ሕግ ፡ "በደጃቸው[5]" ፡ እንዲማሩ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነ ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ትምህርቱ ፡ በቅድሚያ ፡ መሰጠት ፡ ያለበት ፡ በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሁነው ፡ ለሥራቸው ፡ አፈጻጸም ፡ የሕግ ፡ ዕውቀት ፡ ለሚያስፈልጋቸው—ዳኞች ፤ ጠበቆች ፤ የፖሊስ ፡ መኰንኖች ፤ የመንግሥት ፡ ሠራተኞችና ፡ በባንክና ፡ በግል ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የተሰማሩትን ፡ ለመሳሰሉ ፡ እንዲሆን ፡ ተወሰነ ። ይወጣል ፡ የተባለውን ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውሉ ፡ ሊቃውንት ፡ ማግኛ ፡ ዘዴ ፡ ይሀ ፡ ብቻ ነበር ።

### ፪/ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ከምን ፡ ደረጃ ፡ ይሰጥ ?

ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ገና ፡ መጀመሩ ፡ ስለነበረና ፡ ሕግ ፡ ለመማር ፡ የሚገቡ ፡ የኮሌጅ ፡ ዕውቀት ፡ የነበራቸው ፡ ሰዎችም ፡ ስላልነበሩ ፡ ደረጃው ፡ "ከዲግሪ ፡ ዝቅ ፡ ያለ[6]" የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ማቋቋም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነ ። የኮሌጅ ፡ ዕውቀት ፡ ይቅርና ፡ የአሥራ ፡ ሁለተኛን ፡ ክፍል ፡ መልቀቂያ ፡ ፈተና ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ እንኳ ፡ የነበራቸው ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ስለነበሩ ፡ አሥረኛ ፡ ክፍልን ፡ የጨረሱ ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይ ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ የነበራቸው ፡ እንዲገቡ ፡ ተደረገ ። ይህን ፡ እሟልተው ፡ ላልተገኙ ፡ ደግሞ ፡ "በገደብ" እንዲገቡ ፡ ተፈቀደላቸው ። ትምህርቱ ፡ የሚሰጠው ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ስለነበር ፡ ይህንኑ ፡ ቋንቋ ፡ አጣርቶ ፡ ማወቅ ፡ ለሁሉም ፡ አስፈላጊ ።

5. ሕጐቹ ፡ እስኪወጡ ፡ ይጠቅማል ፡ ተብሎ ፡ ባንዳንድ ፡ በኩል ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነውንና ፡ በሁለት ፡ ቋንቋ ፡ የሚሰጠውን ፡ በካናዳ ፡ ውስጥ ፡ የኪውቤክን ፡ ሕግ ፡ ስልት ፡ ጥቂት ፡ የአርትስ ፡ ፋኩልቲ ፡ ምሩቆች ፡ እንዲያጠኑ ፡ ተልከዋል ።

6. አባባሉ ፡ እውጭ ፡ ሀገር ፡ ከተማሩት ፡ ሁለት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በስተቀር ፡ ሌሎችን ፡ ያጠቃልላል ።

## ፫/ ሕጉን ፡ እነማን ፡ ያስተምሩ ?

በሠለጠኑት ፡ ሀገሮች ፡ ውስጥ ፡ መለስተኛ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ የሚያስተምሩት ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ የሚሠሩ ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ወይም ፡ የጠበቆች ፡ ማህበር ፡ አባል ፡ የሆኑ ፡ የሕግ ፡ ባለሙያዎች ፡ ናቸው[7] ። በኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ እንደ ዚህ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ስላልነበሩ ፡ መለስተኛው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ሥር ፡ እየተካሄደ ፡ በተግባራቸው ፡ መምህራን ፡ በሆኑ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ አስተማሪነት ፡ እንዲሰጥ ፡ ሆነ ። በገንዘብ ፡ በኩልም ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ እንደ ፡ አርትስና ፡ ሳይንስ ፡ ፋክልቲዎች ፡ ከኮሌጁ ፡ በጀት ፡ አልነበረውም ። የሕግ ፡ ት/ቤቱ ፡ ሙሉ ፡ ጊዜ ፡ መምህር ፡ "ዲኑ" ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ደሞዙንም ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሲያገኝ ፡ ሌሎቹ ፡ የአርትስ ፡ ፋክልቲ ፡ መምህራን ፡ ሕግ ፡ ት/ቤት ፡ የሚያስተምሩት ፡ በትርፍ ፡ ጊዜያቸው ፡ ሆኖ ፤ ለዚሁም ፡ ሥራቸው ፡ ደሞዝ ፡ የሚያገኙት ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎቹ ፡ ከሚከፍሉት ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ነበር ። ዲኑ ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ በመቃወም ፡ ከጻፋቸው ፡ ብዙ ፡ ደብዳቤዎች ፡ አንዱ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤ "ውጤት ፡ ቢኖረውም ፡ ባይኖረውም ፡ አሁን ፡ ስላለው ፡ አስከፊ ፡ ሁኔታ ፡ እንደገና ፡ አስተያየቴን ፡ መሰንዘር ፡ ግዴታዬ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አምናለሁ ። ሕጎቹን ፡ ለማዘጋጀት ፡ አያሌ ፡ ገንዘብ ፡ ተመድቧል ። ነገር ፡ ግን ፡ የወደፊቱን ፡ ሕጎች ፡ ተረድተው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚችሉ ፡ ዘመናዊ ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ለማፍራት ፡ የሚቻለው ፡ ሦስት ፡ ቋሚ ፡ የሕግ ፡ መምህራን ፡ ሊያስተዳድር ፡ የሚችል ፡ በጀት ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ ቅልብጭ ፡ ያለ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ሲኖር ፡ ብቻ ፡ ነው ።[8]" ነገር ፡ ግን ፡ ስለመምህራን ፡ የተጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ የተፈለገውን ፡ ውጤት ፡ ባለማስገኘቱ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ በዓመት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ ተማሪዎችን ፤ለመቀበልም ፡ ሆነ ፡ ትምህርቱን ፡ ለማፈራረቅ ፡ መቻሉን ፡ ማረጋገጥ ፡ አቃተው ።[9]

## ፬/ የትኛው ፡ ሕግ ፡ ለትምህርት ፡ ይቅረብ ?

ይህ ፡ ከባድ ፡ ጥያቄ ፡ መፍትሔ ፡ የሌለው ፡ መስሎ ፡ ነበር ። ስለዚህም ፡ ጉዳይ ፡ ሬኔ ፡ ዳቪድ ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ሲጽፉ ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፤ "በጣም ፡ አዋቂ ፡ የተባሉት ፡ ሰዎች ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ ማስልጠኛውን ፡ እንደሚያቅዱትና ፡ እንደሚያካሂዱት ፡ በማቅማማት ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ሕግን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የማስተማሩና ፡ የወደፊቶቹን ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ የመመልመል ፡ ዓላማ ፡ ሊሳካ ፡ የቻለው ፡ ሕጎቹ ፡ ተጠቃለው ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅርጽ ፡ በመውጣታቸው ፡ ነው ።[10]"

ከ፲፱፻፵፬—፵፮ ፡ ዓ. ም. ባሉት ፡ ጊዜያት ፡ ውስጥ ፡ ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ የሕጎቹ ፡ መረቀቅ ፡ እንኳ ፡ ያልተጀመረ ፡ በመሆኑ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤቱን ፡ "ጠንካራ ፡ መንፈስ" ከባድ ፡ ችግር ፡ ገጥሞታል ። ባንድ ፡ በኩል ፡ ለጊዜው ፡ የሌለ ፡ ወደፊት ፡ ግን ፡ የሚወጣ ፡ ሕግ ፡ ማስተማር ፡ የማይታለም ፡ ሲሆን ፤ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የጥንቱንና ባሕላዊውን ፡ ሕግ ፡ ከማስተማር ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ አግደውናል ።

---

7. በፈረንሣይ ፡ ሀገር ፡ ግን ፡ ከዲግሪ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ማዕረግ ፡ የሚያስገኙት ፡ "ካፓሲቴ" ኮርሶች ፡ የሚሰጡት ፡ በዩኒቨርስቲው ፡ ውስጥ ፡ ነው ።
8. በ፳፭—፲፪—፲፱፻፵፯ ፡ የተጻፈ ፡ ማስታወሻ ።
9. የኢትዮጵያን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ያረቀቁት ፡ ምሁር ፡ ሬኔ ፡ ዳቪድ ፡ በ፲፬—፲፩—፲፱፻፵፯ ፡ በተጻፈ ፡ ማስታወሻቸው ፡ ገጽ ፡ ፪ ፡ ላይ ፡ በሕግ ፡ ት/ቤቱ ፡ የመምህራን ፡ እጥረት ፡ አሳሳቢ ፡ መሆኑን ፡ ገልጸው ፡ ጽፈዋል ።
10. ሬኔ ፡ ዳቪድ ፡ "የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ" ፡ ራቤልስ ፡ ዚችሪ ፡ ፍት ፡ ፫ል ቶም ፡ ፳ ፡ (፲፱፻፶፫) ፡ ገጽ ፡ ፯፻፷ ።

አንደኛ ፡ ሕጉን ፡ የሚያውቁ ፡ ወይም ፡ በጣሊያንኛና ፡ በግዕዝ ፡ ጽሑፎች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የሕጉን ፡ ርዝራዥ ፡ አንብበው ፡ የሚረዱ ፡ ሰዎች ፡ ቁጥር ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነበር ። በነዚህም ፡ በሁለት ፡ ቋንቋዎች ፡ የተጻፉ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ በሌላ ፡ ቋንቋ ፡ አልተገኙም ። ሁለተኛ ፡ ተማሪዎቻችንን ፡ የጥንቱንና ፡ ባሕላዊውን ፡ ሕግ ፡ ከማስተማርም ፡ ሌላ ፡ ወደፊት ፡ የሚወጡትን ፡ ዘመናዊ ፡ ሕጎች ፡ ከሀገሪቱ ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ አዋህደው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያውሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ከአሁኑ ፡ እንድናዘጋጃቸው ፡ ጠይቀን ፡ ነበር ።[11] እነዚህም ፡ አዲስ ፡ ሕጎች ፡ የፊተኞቹን ፡ የሚሽሩ ፡ ወይም ፡ የሚተኩ ፡ ነበሩ ።[12]

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ዲኑ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ያልደረሰና ፡ ያልታወቀ ፡ ሁኔታ ፡ ገጥሞት ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ወደፊት ፡ የሚወጡት ፡ ሕጎች ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደሆኑ ፡ ፍንጭ ካልተሰጠው ፡ በስተቀር ፡ ለሥራው ፡ አዳጋች ፡ በመሆኑ ፡ ዲንነቱን ፡ እንደሚለቅ ፡ አስታወቀ ። በጥያቄው ፡ መሠረት ፡ የሚወጡት ፡ ሕጎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ "የአውሮፓ ሀገሮች ፡ የሕግ ፡ ስልት" ፡ ላይ ፡ የተጠነሰሱ ፡ ስለመሆናቸው ፡ ተደጋግሞ ፡ ፍንጭ ፡ ተገኘ ።[13] ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ተማሪዎቻችንን ፡ "የሮማውያን" ፡ ሕግ ፡ ስልቶች ፡ ተብለው ፡ ከሚጠሩት ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ሀሳቦች ፤ ምድቦች ፡ አከፋፈሎችና ፡ አስተሳሰቦች ፡ ማለማመድ ፡ አስፈለገ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ እቅድ ፡ ከ፲፱፻፶፯—፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከጥቂት ፡ ስህተት ፡ ጋር ፡ በወጣው ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ ትምህርት ፡ ላይ ፡ ተመልክቷል ።[14] መለስተኛ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ በሚሰጥባቸው ፡ እንደሌሎች ፡ ሀገሮች ፡ ሳይሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ታትሞ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ባለመኖሩ ፡[15] ትምህርቱ ሲጀመር ባቀራረቡ ፡ ያዘነበለው ፡ ሕጉ ፡ በሚሠራበት ፡ ተግባራዊ ፡ ሁኔታና ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ ሳይሆን[16] ፡ ሕግ ፡ በሕብረተ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፤ በምርምር ፤ በታሪክና ፡ በማነፃጸር ፡ መልክ ፡ ሲታይ ፡ ወዳለው ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነበር ።

ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ የማምንቱ ፡ ትምህርት ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፡ ስድስት ፡ ሆኖ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ተኩል ፡ ይፈጅ ፡ የነበረው ፡ የትምህርት ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ ነው ፤

በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመግቢያው ፡ ሰሚስተር ፡ በመጀመሪያ ፡ የቀረቡት ፡ የትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ በሕብረተ ፡ ሰብ ፡ ትምህርት ፤ በታሪክና ፡ በሕግ ፡ ምንነት ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ትምህርቶችና ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ።[17] ሕጎች ፡ በይበልጥ ፡ በሮማውያን ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ስለ ነበሩ ፡ የመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ (፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡) የሕግ ፡ ትምህርት ፡ አትኩሮ ፡ የተመለከተው ፡ በሮማውያን ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ የማነፃፃሪ ፡ ትምህርት ፡ ነበር ። ከተሰጡትም ፡ ሦስቱ ፡ የትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ አንደኛው ፡ የሮማውያን ፡ ሕግ ፡

---

11. የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የትምህርትና ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሪፖርቱ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ ያቀረባቸው ፡ ሃሳቦች ።
12. ለምሳሌ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ሺ፫፻፶፯ ።
13. ከ፲፱፻፶፯—፶፱ ዩ.ኮ. መጽሔት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፶፫ ።
14. ስህተቶቹ ፡ በዲኑ ፡ ማስታወሻ ፡ ቢገለጹም ፡ እንኳ ፡ በስህተት ፡ ማረሚያው ፡ ላይ ፡ አልወጡም ።
15. በክፊል ፡ ካንዳንዶቹ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የዲግሪ ፡ ትምህርት ፡ መመሪያ ፡ ጋር ፡ ይመሳሰላሉ ።
16. የተጠቀሰውን ፡ መጽሔት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፶፮ ፡ ይመለከቷል ።
17. እዚያው ፡ ገጽ ፡ ፩፻፶፪ ።

ዕድገት ፡ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ጋር ፡ ስለነበረው ፡ የጥንት ፡ ዝምድናና ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜም ፡ ስላለው ፡ ቦታ ፡ ነበር ። ሁለተኛው ፡ የመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ትምህርት ፡ ደግሞ ፡ በጀስቲኒያን ፡ መጻሕፍት ፡[18] ውስጥ ፡ በተመለከተው ፡ በሮማውያን ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሆኖ ፡ በዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተቀባይነት ፡ ያገኙትን ፡ ምድቦችንና ፡ ክፍሎችን ፡ ያጠቃልላል ። የሦስተኛው ፡ የመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ትምህርት ፡ ምድብ ፡ ጊዜ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተባለ ፡ ሆኖ ፡ "ከሮማውያን ፡ መሠረተ ፡ ሃሳቦች ፡ (ከጀርመን) የውርስ ፡ ሕግ ፡ እንዴት ፡ እንደመጣ[19]" በሚልና ፡ በመሳሰሉት ፡ አርእስቶች ፡ መነሻሻነት ፡ ስለዘመኑ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መግቢያ ፡ የሚሆኑ ፡ ሃሳቦች ፡ ተሰጥቶበታል ። ሦስቱ ፡ <u>የሁለተኛ ፡ ዓመት</u> ፡ (፲፱፻፵፮) ዓ ፡ ም ፡ የትምህርት ፡ ምድቦች ፡ ደግሞ ፡ ተማሪዎቹን ፡ ከኢንተርናሽናል ፡ ሕግ ፤ አስፈላጊ ፡ ከሆኑት ከወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረታዊ ፡ አስተሳሰቦችና ፤ «የፍትሐ ፡ ብሔር ሕግን ፡ ለመተንተንና ፡ ለመማር» ፡[20] መግቢያ ፡ ከሚሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ጋር ፡ አስተዋውቋቸዋል ። ወደፊት ፡ ለሚወጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አምሳያ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ ለተገመተው ፡ ለሮማውያን ፡ የሕግ ፡ ስልት ፡ ትምህርት ፡ የመጨረሻ ፡ ለሆነው ፡ በዚህ ፡ የትምህርት ፡ ዘመን ፡ አንዳንድ ፡ ሕጋዊ ፡ ጉዳዮችን ፡ ተንትኖ ፡ እልባታቸውን ፡ በመሻት ፡ ረገድ ፡ ይረዳ ፡ ዘንድ ፡ ለማስተማርያ ፡ የተመረጠው ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቅጅ ፡ የነበረን ፡[21] የግብጽ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ተማሪዎቹ ፡ ወደፊት ፡ የሚወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሲውል ፡ የሚያጋጥማቸውን ፡ አንዳንድ ፡ ችግሮች ፡ በቅድሚያ ፡ ማወቅ ፡ ችለዋል ። <u>በሦስተኛው ፡ ዓመት</u> ፡ (፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡) በወንጀል ፡ ጉዳይ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ ፕሬዚዳንትና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳይ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ፡ የሚያወጣቸው ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕጎች ፡ እያደር ፡ ብቅ ፡ እያሉ ፡ በመሄዳቸው ፡ በነዚሁ ፡ ሕጎች ፡ ላይ ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ትምህርት ፡ መስጠት ፡ ተቻለ ። በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ሁለተኛው ፡ ምድብ ፡ ትምህርት ፡ ደግሞ ፡ ለተከታዩ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ መሠረት ፡ ለመጣል ፡ ታስቦ ፡ በጥቂቱ ፡ የኢኮኖሚክስ ፡ ትምህርት ፡ ተከሎበት ፡ ነበር ።[22] ስለ ፡ አውሮፓ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ መንሥኤ ፤ ዕድገትና ፡ ግልጋሎት ፡ መግለጫ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ ትምህርቱ ፡ በይበልጥ ፡ የሚያተኩረው ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ተቀባይነትን ፡ ባገኙ ፡ ሕጎች ፡ ወይም ፡ በወደፊቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተቀባይነትን ፡ ያገኛሉ ፡ ተብለው ፡ በታሰቡ ፡ የሕግ ፡ ረቂቆች ፡ ላይ ፡ ነበር ። በመጨረሻም ፡ የሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ትምህርት ፡ በሕግ ፡ አርእስት ፡ ላይ ፡ የክርክር ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፡ ነበረው ።[23] በዚያ ፡ ክፍለ ፡ ጊዜያት ፡ ውስጥ ፡ ከቀረቡት ፡ ክርክሮች ፡ ተፈራ ፡ ደገፌ ፡ (የአሁኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግድ ፡ ባንክ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ) "በኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ መነሻ ፡ ገንዘብ ፡ ስለማከማቸት" ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ያዘጋጁት ፡ ጽሑፍ ፡ ወደር ፡ ያልነበረው ፡ መሆኑንና ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅም ፡ አሳትሞት ፡ እንደነበር ፡ በአጋጣሚው ፡ መጥቀስ ፡ ይገባል ። ያም ፡ እትም ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ያህል ፡ በኮሌጅ ፡ ተማሪ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በመጽሐፍ ፡ መልክ ፡ የቀረበ ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ቆይቷል ።

---

18. እዚያው ፤ ገጽ ፡ ፩፻፵፫ ።
19. እዚያው ፤ ገጽ ፡ ፩፻፵፫ ።
20. እዚያው ፤ ገጽ ፡ ፩፻፵፮—፵፰ ።
21. ትምህርት ፡ ይሰጥበት ፡ የነበረውን ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተማሪዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ማወቃቸው ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ ነበር ።
22. እዚያው ፡ ገጽ ፡ ፩፻፶፯—፶፰ ።
23. እዚያው ፤ ገጽ ፡ ፻፵፯ ።

## ፭/ ሌሎች ፡ ድርጊቶች ።

በሳምንት ፡ ከሚሰጡት ፡ ስድስት ፡ ክፍለ ፡ ጊዜያት ፡ አራቱን ፡ በተከታታይ ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ መምህር ፡ የሆኑት ፡ ዲኑ ፡ ሲያስተምሩ ፡ ሁለቱ ፡ ደግሞ ፡ የሚሰጡት ፡ በትርፍ ፡ ጊዜአቸው ፡ በሚያስተምሩ ፡ በሁለት ፡ መምህራን ፡ ነበር ። ትምህርቱ ፡ የሚቀርበው ፡ በዲስኩር ፡ መልክ ፡ ሆኖ ፡ በመጨረሻም ፡ ጥያቄ ፡ ይቀጥልና ፡ አከራካሪ ፡ በሆኑ ፡ ነጥቦች ፡ ላይ ፡ የሞቀ ፡ ውይይት ፡ ይደረጋል ።

ከሮማውያን ፤ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፤ ከወንጀለኛና ፡ ከንግድ ፡ ሕግ ፡ እንዲሁም ፡ ከሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግና ፡ ከኢኮኖሚክስ ፡ ትምህርቶች ፡ ተመርጠው ፡ የተውጣጡ ፡ ጥያቄዎች ፡ ያለበትና ፡ የማለፊያውን ፡ ፈተና ፡ ግማሽ ፡ ዋጋ ፡ የያዘ ፡ አጠቃላይ ፡ ፈተና ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተሰጥቶ ፡ የትምህርቱ ፡ ዘመን ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ ። በየካቲት፡ ወር ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ለመግባት ፡ ከመለከቱት ፡ ፩፻፳፩ ፡ ተማሪ ዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ፴፱ ፡ ትምህርቱን ፡ በሚገባ ፡ ፈጽመው ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የተሰጠውን ፡ የሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ ለማግኘት ፡ በቅተዋል ።[24]

## ፮/ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ጉድለቶች ።

የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ብዙ ፡ ጉድለቶች ፡ ነበሩት ፡ ከነዚያም ፡ ጥቂቶቹ ፡ ሊወገዱ ፡ የማይቻሉ ፡ ሲሆኑ ፡ ሌሎቹ ፡ ግን ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ አመራር ፡ ምክንያት ፡ የተ ፈጠሩ ፡ ነበሩ ።

### ሊወገዱ ፡ የማይችሉት ፡ ጉድለቶች ፡

ሀ/ የተማሪዎቹን ፡ መደበኛ ፡ ሥራ ፡ ላለማጨናጐል ፡ ሲባል ፡ የትምህርቱን ፡ ጊዜ ፡ በማታ ፡ ብቻ ፡ መወሰኑ ፤[25]

ለ/ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በተማሪዎች ፡ ላይ ፡ የሚታይባቸው ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ የመሠረታዊ ፡ ቀለም ፡ ትምህርት ፡ ማነስ ፤[26]

ሐ/ ትምህርቱ ፡ በሚሰጥበት ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ የተዘጋጁና ፡ ለትምህርቱ፡ አግባብ ፡ ያላቸው ፡ የአውሮፓውያን ፡ የትምህርት ፡ መሣሪያዎች ፡ አለመ ገኘት ፤ ናቸው ።

---

24. ስማቸው ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። አበበ ፡ ተፈራ ፤ አሸናፊ ፡ ቤተ ፡ ማርያም ፤ አሰፋ ፡ ፀጋዬ ፤ አጥናፌ ፡ ፀሐይ ፤ በቀለ ፡ ኃ/ሚካኤል ፤ በየነ ፡ ወ/ማርያም ፤ ዳዊት ፡ ገብሩ ፤ አገታ ፡ ፈይሣ ፡ ባልቻ ፤ ኢያሱ ፡ ገ/ ሕይወት ፤ ፈቀታ ፡ ሥላሴ ፡ ጌታሁን ፤ ገብሬ ፡ ወዳጆ ፤ ሃይሉ ፡ ገጋው ፤ ኃ/ማርያም ፡ ወ/ኪዳን ፤ ሕይወት ፡ ሕዳሩ ፤ ሆቨኖስ ፡ ካይፓኒያን ፤ ቀንአ ፡ ቱማ ፤ ካሣ ፡ በየነ ፤ ከበደ ፡ ገ/ማርያም ፤ ኪዳነ ፡ ማሾ ፤ ለገሠ ፡ ወ/ሐና ፤ ለማ ፡ ፈይሣ ፤ መብራቱ ፡ ፍስሐ ፤ መሐመድ ፡ ብድሪ ፤ ነጋሽ ፡ ደነቀ ፤ ፓንዲት ቢ ፡ ጂ ፤ ሰሜይ ፤ ተክሉ ፤ ሻምሱ ፡ አህመድ ፤ ሽፈራው ፡ አማረ ፤ ስለሺ ፡ ድፋባቸው ፤ ታደሰ ፡ ድልነሣሁ ፤ ታደሰ ፡ መንገሻ ፡ ተፈራ ፡ ደግፌ ፤ ጥበቡ ፡ በየነ ፤ ተፈራ ፡ ለማ ፤ ጥላሁን ፡ ብሩ ፤ ወርቁ ፡ በሻዬ ፤ ዘውዱ ፡ መኰንን ፤ ዘነበ ፡ ወርቅ ፡ ኃይሌ ።

ልዩ ፡ ልዩዎቹን ፡ የመጀመሪያውን ፡ የሕግ ፡ ኮርስ ፡ በተከታታይ ፡ ሲያስተምሩ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ጂስማን ፤ ሩስኪ ፤ ቼቼኖቪች (ከመጀመሪያውኑ ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ መምህር) ከሩኪ ፤ ግራቨስኪና ፡ ሮበርትስ ፡ ናቸው ።

25. ከላይ ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፱ ፡ ይመለከቷል ።

26. ከላይ ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፰ ፡ ይመለከቷል ።

ይህ ፡ ሦስተኛው ፡ ጉድለት ፡ ከሁሉም ፡ የበለጠ ፡ ችግር ፡ ፈጥሮ ፡ ነበር ። ለመግ ቢያው ፡ ሰሚስተር ፡[27] በክፊል ፡ የሚበቁና ፡ ከዚያም ፡ ቀጥሎ ፡ ለሮማውያን ፤ ለኢንተ ርናሽናል ፡ ሕግና ፡ ለኢኮኖሚክስ ፡ ትምህርት ፡ ማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ የተዘጋጁ ፡ በቂ ፡ የማስተማሪያ ፡ መሣሪያዎች ፡ ነበሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ዝርያቸው ፡ ከአውሮፓውያን ፡ የሕግ ፡ ቅንጅት ፡ ሆኖ ፡ ለሚዘጋጁት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የወንጀለ ኛና ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ መደበኛ ፡ ትምህርት ፡ ማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ በእን ግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ባለመገኘታቸው ፤ መምህራኑ ፡ "ከፈረንሣይ ከስዊስና ፡ ከጀርመን ፡ የሕግ ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ መርጠው ፡ እፁብ ፡ ድንቅ ፡ በሆነ ፡ ቅልጥፍና ፡ ለሕግ ፡ አነጋ ገር ፡ በማይመች ፡ በእንግሊዝኛ ፡ አነጋገር ፡ በመተርጐም ፡ ተጠቅመውባቸዋል ። በዚ ኸም ፡ የቋንቋ ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ ማስተማሪያና ፡ ማገናዘቢያ ፡ ይሆናሉ ፡ የተባሉትን፡ የመጀመሪያዎቹን ፡ መጻሕፍት ፡ ሕግ ፡ "የማያነቡት" ፡ ተማሪዎች ፡ ሊጠቀሙባ ቸው ፡ አልቻሉም ።"[28] እንዲጋጣሚ ፡ የሕግ ፡ አስተማሪዎቻችን ፡ የሚያስተምሩትን ፡ ሕግ ፡ ስልትና ፡ ቋንቋ ፡ (ጣልያንኛም ፡ ጭምር) ፡ ያውቁ ፡ ስለነበር ፡ ይህን ፡ ከባድ ፡ ችግር ፡ የሚጠበቅባቸውን ፡ ያህል ፡ ሊያቃልሉት ፡ ችለዋል ።

<u>ሌላው</u> ፡ ለሕግ ፡ ት/ቤት ፡ መዳከም ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ አመራር ፡ ነበር ።[29] ይህም ፡ በጣም ፡ ጐልቶ ፡ የታየው ፡ እላይ ፡ የተወሳለት ፡ የመጀመ ሪያው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ሲሆን ፡ ቀደም ፡ ብሎም ፡ ት/ቤቱን ፡ ለማሻሻል ፡ ስለበጀት ፤ ስለተጨማሪ ፡ አስተማሪ ፤ ስለተማሪዎች ፡ መቀበያና ፡ የኮርስ ፡ መለዋወጫ ፡ ጊዜ ፡ ወዘተ ፡ ዲኑ ፡ ያቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ሳያገኝ ፡ በአንጻሩ ፡ ግን ፡ የሌሎቹ ፡ ኮሌጆች ፡ ቅርንጫፎች ፡ በተፋጠነ ፡ ሁኔታ ፡ ሲስፋፉ ፡ ታይተዋል ።

## ፯/ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ያስገኘው ፡ <u>ፍሬ</u> ።

የተጠቀሱት ፡ የአመራርና ፡ ሌላም ፡ ጉድለቶች ፡ ቢኖሩም ፡ እንኳ ፡ የመጀመሪ ያው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ አጀማመሩ ፡ ተስፋ ፡ ያለው ፡ ነበር ። የሚሰጠው ፡ ትምህርት፡ ሁሉንም ፡ አጠቃላይና ፡ ዘዴ ፡ ያለው ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የተመራቂዎቹም ፡ ቁጥር ፡ የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ አር ፡ ዳቪድ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ በዓመት ፡ «አርባ" የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማስመረቅ ፡ ይኖርበታል ፡ ካሉት ፡ ጋር ፡ የተቀራረበ ፡ ነበር ።[30] ሌሎች ፡ ባለሙያዎችና ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴርም ፡ በሥራችን ፡ መደሰታቸውን ፡ ገልጸውልናል ። የትርፍ ፡ ጊዜ ፡ መምህራን ፡ ከሚገባቸው ፡ ማርክ ፡ በላይ ፡ ሰጥተው ፡ ካሳለፉአቸው ፡ ጥቂት ፡ ተማሪዎች ፡ በስተቀር ፡ የምርቃት ፡ ደረጃ ፡ "ካፖሲቴ" ፡ ከተባለው ፡ የፈረን ሣይ ፡ መለስተኛ ፡ የሕግ ፡ ደረጃ ፡ ጋር ፡ ተመጣጣኝ ፡ ነበር ። ደግሞም ፡ በክ ፍል ፡ ውስጥ ፡ ይሰጥ ፡ የነበረው ፡ የሕግ ፡ ክርክርና ፡ የምርምር ፡ ትምህርት ፡ የተራቀቀ፡ መጽሐፍ ፡[31] ለመጻፍና ፡ ለማተም ፡ ምክንያት ፡ ሆኗል ። ከተመረቁትም ፡ ጥቂቶቹ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የኃላፊነት ፡ ሥራ ፡ ተሰጥቷቸዋል ። (ለምሳሌ ፡ አምስቱ ፡ የጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡

---

27. የተጠቀሰውን ፡ መጽሔት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፵፪ ፡ ይመለከታል ።
28. ጂ. ቼቼኖቪች "የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት" "የኢትዮጵያ ፡ ጥናት ፡ መጽሔት ።"አንደኛ፡ ቮል ዩም ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ገጽ ፡ ፷፱ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ትምህርትና ፡ ወይም ፡ ለንባብ ፡ የሚ ሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ ከ፲፱፻፶፰—፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ በወጡት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዩ.ኮ. መጽሔቶች ፡ ተጠ ቅሰዋል ።
29. ከታች ፡ ይመለከቷል ።
30. የ፲፩—፲፩—፶፯ ፡ ማስታወሻ ።
31. እላይ ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፶፯ን ፡ ይመለከቷል ።
እታች ፡ ይመለከቷል ።

ቤት ፡ ዳኞች ፡ ሲሆኑ ፡ አንዱ ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ፡ ሆነዋል) ። ጥቂቶቹ ፡ ደግሞ ፡ በይበልጥ ፡ ዕውቀታቸውን ፡ ለማሻሻል ፡ በማሰብ ፡ ከ፲፱፻፶፮—፷፩ ዓ ፡ ም ፡ ሲሰጥ ፡ የነበረውን ፡ ከፍተኛ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ተሳትፈዋል ።[32]

## ለ/ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ መታገድና ፡ (፲፱፻፶፰ ዓ ፡ ም ፡)

## "የሕግ ፡ ፋክልቲው" ፡ ችግር ፡ (ከ፲፱፻፶፰—፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡)

የመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ አዳዲስ ፡ የትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ ስለሚጀመሩበት ፡ ሁኔታ ፡ ዲኑ ፡ በዛ ፡ ያሉ ፡ ሃሳቦችን ፡ አቅርቦ ፡ ነበር ። ሬኔ ፡ ዳቪድ ፡ ያሉትን ፡ በዓመት ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ አርባ ፡ የሕግ ፡ ምሩቃን ፡ ለማፍ ራት ፡ የሚያስችለው ፡ በየዓመቱ ፡ ተማሪዎችን ፡ የመቀበሉ ፡ ፕሮግራም ፡ በመማሪያና ፡ በመምህራን ፡ እጥረት ፡ የተነሣ ፡ ያልተሳካ ፡ በመሆኑ ፡ ዲኑ ፡ ተማሪዎችን ፡ የመቀበሉ ፡ ጉዳይ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሆን ፡ እለበለዚያም ፡ የመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ እንደተፈጸመ ፡ ወዲያውኑ ፡ መሠረታዊ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ማስ ተማሩ ፡ እንዲጀመር ፡ በማለት ፡ አጥብቆ ፡ አሳስቦ ፡ ነበር ። በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለሕግ ፡ ዲግሪ ፡ የሚያበቃ ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጥበት ፡ የሕግ ፡ ኮሌጅ ፡ ይከፈታል ፡ በሚል ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ እምነት ፡ ምክንያት ፡ የተነሳ ፡ የቀረበው ፡ ማሳሰቢያ ፡ ተቀባይነት ፡ ሳያ ገኝ ፡ ከመቅረቱም ፡ ሌላ ፡ ት/ቤቱ ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተዘጋ ።[33] የት/ቤቱ ፡ መዘጋት ፡ ያስከተለው ፡ ውጤት ፡ ያስተምሩ ፡ የነበሩትን ፡ ጥቂት ፡ መምህራን ፡ የማስተማር ፡ ችሎታ ፡ ማባከን ፡ ብቻ ፡ ነበር ።[34]

እነዚህ ፡ ሳይብራሩ ፡ የቀሩትና ፡ የሕግ ፡ ት/ቤትን ፡ የሚመለከቱት ፡ ውሳኔዎች ፡ የተደረጉት ፡ የሕግ ፡ ዕውቀት ፡ የሌላቸው ፡ የኮሌጁ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የሕግ ፡ ምሁራንን ፡ ሀሳብ ፡ ሳይጠይቁ ፡ ወይም ፡ ምክር ፡ ሳይሹ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ስለሕግ ፡ መሃይም ፡ የሆኑ ትን ፡ የአርትስ ፡ ኮሌጅ ፡ ዲን ፡ ካማከሩ ፡ በኋላ ፡ ነበር ። በአመራር ፡ ረገድ ፡ ኮሌጁ ፡ በሌላው ፡ ትምህርት ፡ መስክ ፡ ምስጋናን ፡ ያተረፈ ፡ በመሆኑ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ያሳየው ፡ ዝንባሌ ፡ ለመረዳት ፡ ምክንያት ፡ ቢያሻ ፡ ኮሌጁ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመምራት ፡ የሚችሉና ፡ የተማሩ ፡ ሰዎች ፡ ለማዘጋጀት ፡ ላለው ፡ ቁርጥ ፡ ሃሳብ ፡ ቅድ ሚያ ፡ በመስጠትና ፡ እንደነዚህ ፡ ዓይነቱን ፡ ሰዎች ፡ መለስተኛ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ በመስጠት ፡ ማግኘት ፡ እንደማይቻል ፡ በማመት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ይቻላል ።[35] (ግን ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፶፭ ፡ ይመለከቷል) ። የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ መቋረጥ ፡ ወይም ፡ በጠ ባብ ፡ ተወስኖ ፡ መቅረት ፡ ስለተነቀፈና ፡ የእኛም ፡ ስምና ፡ ዝና ፡ ስለጐደፈ ፡ ከ፲፱፻፶፰— ፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ዲግሪ ፡ የሚሰጥበት ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ለማቋቋም ፡ ከጸጸት ፡ ጋር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዝግጅቶች ፡ ተጀመሩ ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ እቅድ ፡ የተወጠነው ፡ ት/ቤቱ ፡ አጥጋቢ ፡ ውጤት ፡ እንዲሰጥ ፡ የሚያስችሉት ፡ ተቀዳሚ ፡ ነገሮች ፡ ባልነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ መሆኑን ፡ የተገነዘቡት ፡ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ የተመረቁት ፡ ሲቃውንት ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ።

ከ፲፱፻፶፰—፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በነበረው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤቱ ፡ ዲን ፡ የተጠ የቀውን ፡ የወደፊት ፡ የዲግሪ ፡ ፕሮግራም ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ አመቺ ፡ ባል

32. በገዥው ፡ (በአስተዳዳሪው ፡ ቦርድ) ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲን ፡ ለማቋቋም ፡ የሚያስችሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ተጠንተው ፡ ነበር ። ቦርዱ ፡ ከዲግሪ ፡ ዝቅ ፡ ያለው ፡ ኮርስ ፡ እንዲቋረጥ ፡ ወይም ፡ የተወሰነ ፡ ወይም ፡ እንደሆን ፡ አልጠየቀም ።

34. የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ እንደዚህ ፡ ባለው ፡ አመራር ፡ ሊደሰት ፡ አልቻለም ፡ ከ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮም ፡ የዲኑን ፡ ደመወዝ ፡ መክፈል ፡ ስላቋረጠ ፡ ኮሌጁ ፡ የበለጠ ፡ የበጀት ፡ ሸክም ፡ ደረሰበት ።

35. ለምሳሌ ፡ የ፲፱፻፶፪—፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዩ.ኮ. መጽሔት ፡ ገጽ ፡ ፳፫ ፡ ይመለከቷል ።

ሆነ ፡ ጊዜ ፡ በዲግሪ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ለመስጠት ፡ ፈቃደኛ ፡ አለመሆኑን ፡ በመደጋገም ፡ ገልጿል ።[36] ምክንያቱም ፡ (፩) የሚሰጠው ፡ ትምህርትና ፡ (፪) የሚማሩ ፡ እጩዎች፡ ሳይኖሩ ፤ (፫) ት/ቤቱ እራሱን ፡ የቻለ ፡ የአስተዳደር ፡ መብት ፡ ሳያገኝ ፡ ፕሮግራሙ ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ፡ በሚል ፡ እምነት ፡ ነበር ። ይኸም ፡ ማለት ፤

፩/ የአንድ ፡ ሀገር ፡ ሕግ ፡ ገና ፡ ሳይወጣ ፡ ወይም ፡ ገና ፡ ሳይታወጅ ፡ (ይህም ፡ ቢቀር ፡ ገና ፡ ሳይታተም) ለሙሉ ፡ ጊዜ ፡ የዲግሪ ፡ ፕሮግራም ፡ ተማሪዎች፡ ስለሕጉ ፡ ትምህርት ፡ መስጠት ፡ አይቻልም ።[37] ይህ ፡ ተቃውሞ ፡ በቂ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በተጨማሪ ፡ የሚከተሉት ፡ ምክንያቶች ፡ ነበሩ ።

፪/ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ የዲግሪ ፡ ፕሮግራም ፡ መለስተኛ ፡ የኮሌጅ ፡ ትምህርት ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይ ፡ ትምህርት ፡ ያላቸው ፡ እጩዎች ፡ እንዲቀርቡለት ፡ ያስፈልጋል ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉ ፡ የዲግሪ ፡ ፕሮግራም ፡ ለማቋቋም ፡ የሚያስችሉ ፡ እጩዎች ፡ ለማቅረብ ፡ አልቻለም ።

፫/ የሕግ ፡ ሙያ ፡ የሚያሳትፍ ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ ከአርትስ ፡ ፋክልቲ ፡ በሚገኙ ፡ የትርፍ ፡ ጊዜ ፡ አስተማሪዎች ፡ እርዳታ ፡ መመስረት ፡ ብቁ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ምክንያቱም ፡ የአርትስ ፡ ፋክልቲና ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ የትምህርት ፡ አሰጣጥ ፡ ዘዴና ፡ ዓላማ ፡ በጣም ፡ የተለያዩ ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ። የሕግ ሙያን ፡ የሚያስተምር ፡ ፋክልቲ ፡ በበጀት ፡ መምህራን ፡ በመምረጥና ፡ መጽሐፍትን ፡ በመግዛት ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ ካላስተዳደረ ፡ እያደገ ፡ ሊሄድ ፡ አይችልም ።

እላይ ፡ የተመከቱት ፡ ችግሮች ፡ በሕግ ፡ ለተመረቁት ፡ ሰዎች ፡ ግልጽ ፡ ነበሩ ። ሆኖም ፡ በፕሬዚዳንቱ ፡ ወይም ፡ በአርትስ ፡ ፋክልቲ ፡ ዲን ፡ ዘንድ ፡ ጊዜው ፡ የማይፈቅድለትን ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ ማቋቋም ፡ ዓላማ ፡ በየጊዜው ፡ እያንሠራራ ፡ በመጨረሻው ፡ የዲግሪ ፡ ፕሮግራሙ ፡ እስኪጀመር ፡ ድረስ ፡[38] በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ጨርሶ ፡ መዘጋት ፡ አስከተለ ። የዲግሪው ፡ ፕሮግራም ፡ እስኪጀመር ፡ ጥበቃው ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ በመፍጀቱ ፡ በዲግሪም ፡ ሆነ ፡ ከዚያ ፡ ባነሰ ፡ ደረጃ ፡ ተምረው ፡ ሀገራቱን ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ ሊጠቅሙ ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ ባለመማራቸው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ከባድ ፡ ጉዳት ፡ ሳያስከትል ፡ አልቀረም ።

## ሐ/ የሕግ ት/ቤት ከፍተኛ ኮርስ (፲፱፻፶፬—፷፩)

የሕግ ፡ ት/ቤቱ ፡ በ፲፱፻፶፫ ዓ ፡ ም ፡ ለዓመት ፡ ያህል ፡ ከተቋረጠ ፡ በኋላ ፡ ከዲግሪ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ማዕረግ ፡ የሚያሰጥ ፡ መሠረታዊ ፡ አዲስ ፡ ኮርስ ፡[39] እንዲጀመርና ፡ የተቋረጠው ፡ የመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ኮርስ ፡ ምሩቃን ፡ ለነበሩት ፡ ከፍተኛ ፡ የሕግ ፡ ትም

---

36. ከዲግሪ ፡ ዝቅ ፡ ያለው ፡ ኮርስ ፡ ሲቋረጥ ፡ ወይም ፡ የተወሰነ ፡ ሲሆን ፡ ሥራቸውን ፡ ለመልቀቅ ፡ ደጋግመው ፡ ጠይቀዋል ፤ ግን ፡ የሚተካቸው ፡ አልነበረም ።

37. በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እዚያ ፡ ደረጃ ፡ የደረሰው ፡ አዲሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ የወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ደግሞ ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ደርሷል ።

38. አክሲሉ ፡ ሀብቴ ፡ "የአዲስ ፡ አበባ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ታሪክ ፡ አጭር ፡ መግለጫ" "የዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ መግለጫ" (፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፴፩ ፡ በቍጥር ፡ የተጠቀሰ ፡ (እላይ ፡ በ፳፰ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ የተጠቀሰ) ፡ ገጽ ፡ ፳፰

39. እታች ፡ በ(መ)ሥር ፡ ይመለከቷል ።

ሀርት ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ስምምነት ፡ ተደረገ ፡፡ ይህም ፡ እንዲሆን ፡ ያስቻለው ፡ በተለይ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ማውጣትና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የመጨረሻ ፡ ረቂቆች ፡ መገኘት ፡ ነው ፡፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ግን ፡ ከፍተኛውን ፡ ኮርስ ፡ ለሚወስድ ፡ የፈለጉትን ፡ የመጀመሪያው ፡ ኮርስ ፡ ምሩቃን ፡ (ማለፊያው ፡[60%] ቢሆንም ፡ እንኳ ፡) ከ[60%—65%] ያገኙትን ፡ እንዳይገቡ ፡ ከለከሉ ፡፡[40] በዚህ ፡ ተስፋ ፡ እስቆራጭ ፡ አመራር ፡ ምክንያት ፡ አስራ ፡ አምስት ፡ ምሩቃን ፡ ብቻ ፡ ለከፍተኛው ፡ ኮርስ ፡ ገቡ ፡፡ ከነዚህም ፡ አስራ ፡ ሁለቱ ፡ የከፍተኛውን ፡ ኮርስ ፡ ዲፕሎማ ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አገኙ ፡፡[41] እነዚህ ፡ አስራ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ አዲስ ፡ የተገኙትን ፡ ሕጎች ፡[42] በተጨማሪ ፡ ለአንድ ፡ ዓመት ፡ ቆይተው ፡ በ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንዲማሩ ፡ ለሚለው ፡ ሀሳብ ፡ አልተበገሩለትም ፡፡

በከፍተኛው ፡ ኮርስ ፡ በተለይ ፡ የሚሰጡት ፡ ትምህርቶች ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ስለ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡[43] ስለ ፡ መንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ነበር ፡፡ የከፍተኛው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ኮርስ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቅርንጫፎች ፡ የሚወጡትን ፡ ንድፍ ፡ ሕጎች ፡ እየተከታተለ ፡ ሲሰጥ ፡[44] የከፍተኛው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ኮርስ ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ይተነትን ፡ ነበር ፡፡[45] በኢኮኖሚክስ ፡ ትምህርት ፡ ጊዜ ፡ ባጭሩ ፡ ሲሰጥ ፡ የነበረው ፡ ስለመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ የሚመለከተው ፡ ኮርስ ፡ ደግሞ ፡ አሁን ፡ በከፍተኛው ፡ ኮርስ ፡ ጊዜ ፡ በቅርቡ ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ መሠረት[46] ፡ ከባድና ፡ በጣም ፡ ዝርዝር ፡ በሆነ ፡ ሆኖቹ ፡ ይሰጥ ፡ ነበር ፡፡ በተወግዜም ፡ አስተማሪዎች ፡ እንደ ፡ አማካሪዎች ፡ ብቻ ፡ ሆነው ፡ እየሠሩ ፡ የክርክሩ ፡ ክፍል ፡ እንደትርፍ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ተቀጥሮ ፡ እንዲቀጥል ፡ ተደረገ ፡፡

## መ/ ሁለተኛው ፡ መሠረታዊ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ኮርስና ፡ የት/ቤቱ ፡ መዘጋት ፡ (ከ፲፱፻፷፬—፷፰ ዓ ፡ ም፡)

ለመጀመሪያዎቹ ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ (ከ፲፱፻፷፬—፷፭ ፡ ዓ. ም.) ሁለተኛው ፡ መሠረታዊ ፡ የሕግ ፡ ኮርስ ፡ ለወትሮ ፡ ተማሪዎች ፡ ሲሰጥ ፡ ከነበረው ፡ ከከፍተኛው ፡ ኮርስ ጋር ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ይመራ ፡ ነበር ፡፡ በመጨረሻም ፡ የትርፍ ፡ ጊዜ ፡ አስተማሪዎች ፡[47] ያለባጀት ፡ ድጋፍ ፡ ማግኘት ፡ ተችሏል ፡፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ የነበረው ፡

40. ዲኑ ፡ መግቢያው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ እንዲሆን ፡ ቢፈልግም ፡ አልሆነም ፡፡ የሕግ ፡ ት/ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ የሚሰጠውን ፡ የትምህርት ፡ ዓይነት ፡ ማዘጋጀት ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡፡ ዲኑም ፡ ለስም ፡ የተቀመጠ ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ አልነበረም ፡፡

41. ስማቸው ፡ እንደሚከተለው ፡ ነበር ፡፡ አሸናፊ ቤተ ፡ ማርያም ፤ አሰፋ ፡ ፀጋዬ ፤ ንጥናፌ ፡ ፀሐይ ፤ በቀለ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፤ ፈቀደ ፡ ሥላሴ ፡ ጌታሁን ፤ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ወልደ ፡ ኪዳን ፤ ካሣ ፡ በየነ ፤ ለማ ፡ ፈይሣ ፤ መብራቱ ፡ ፍስሐ ፤ ጥበቡ ፡ በየነ ፤ ተፈራ ፡ ለማ ፤ ወርቁ ፡ በሻየ ፡፡

አስተማሪዎቹ ፡ ደግሞ ፡ ሮቺኖቪች ፡ (የሙሉ ፡ ጊዜ) ፡ ማራቭውስኪና ፡ ስታንሊ ፡ ነበሩ ፡፡

42. ለነሱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ በኩሌጁ ፡ መማክርት ፡ የፈረሰው ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ ሊሰጣቸው ፡ ቃል ፡ የገቡላቸው ፡ ነበር ፡፡ (በኋላም ፡ ይኸው ፡ "ከ፷፭ ፡ በመቶ ፡ በታች" ያገኙ እንዳይገቡ ፡ ለመከልከል ፡ ምክንያት ፡ ሆኗል ፤ እላይ ፡ ይመለከቷል ፡፡)

43. ይህ ፡ የወጣው ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ነበር ፡፡

44. (በ፲፱፻፷፰—፱ ፡ ዓ. ም. ዩ.ኮ. መጽሔት ፡ ገጽ ፡ ፶፬) ፡ በመንግሥቱ ፡ አስተያየት ፡ ረቂቆቹ ፡ ምስጢር ፡ ስለነበሩ ፡ ለማግኘት ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበር ፡፡

45. እዚያው ፡ ገጽ ፡ ፻፳፰ ፡፡

46. እዚያው ፡፡

47. እላይ ፡ ሀ/ን ፡ ይመለከቷል ፡፡

የኮሌጁ ፡ ተስፋ ፡ አስቆራጭ ፡ አመራር ፡ እንደ ፡ ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡[48] "ብዙ" እጩ ዎች ፡ እንዲቀርቡ ፡ አደረገ ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ወደ ፡ ት/ቤቱ ፡ ለመግባት ፡ የሚያስች ለው ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ በማለቱ ፡ የሚገቡት ፡ ተማሪዎች ፡ ቁጥር ፡ የተወሰነ ፡ ሆነ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ት/ቤቱ ፡ ለመግባት ፡ ብቁ ፡ ሆኖ ፡ ለመገኘት ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ ሁለተኛ ፡ ክፍል ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይ ፡ ትምህርት ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ ልምምድ ፡ እንዲኖረው ፡ ከማስፈለጉም ፡ በላይ ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ችሎታውን ፡ የሚያ ሳይ ፡ ፈተና ፡ ወስዶ ፡ ማለፍ ፡ ነበረበት ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የገቡት ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ብቻ ፡ ሲሆኑ ፡ ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ ስምንቱ ፡ ብቻ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለመመረቅ ፡ በቁ ።[49]

በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መታወጅና ፡ አድናቆትን ፡ ያተረፈው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንዳንድ ፡ እያለ ፡ በጥራዝ ፡ መልክ ፡ መውጣት ፡ ኮርሱን ፡ ሊጠቅም ፡ ችሏል ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የአሁኑ ፡ ትምህርት ፡ ከ፲፱፻፵፬— ፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲሰጥ ፡ ከነበረው ፡ ከመጀመሪያ ፡ የሕግ ፡ መሠረታዊ ፡ ኮርስ ፡ የተለየ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ መግለጫ ፡ ለሦስት ፡ ዓመታት ፡ በሳምንት ፡ ስድስት ፡ ጊዜ ፡ ሲሰጥ ፡ ስለነበረው ፡ ትምህርት ፡ ነው ።

በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ (፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ሦስት ፡ ኮርሶች ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ። የ"ቲዩረቲካል ፡ ኢንትሮዳክሽን ፡ ቱ ፡ ሎው ፡" ማለትም ፡ "ለሕግ ፡ መግቢያ ፡ የቲዩሪ ፡ ትምህርት ፡" የሚባለው ፡ ኮርስ ፡ ተማሪዎቹን ፡ ከሕግ ፡ አስተሳሰብ ፤ (Juris Prudence) ከሕግ ፡ ምንጮችና ፡ ሕግን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ከሚረዱ ፡ ዕውቀቶች ፡ ጋር ፡ አለማመዳቸው ። "ሒስቶሪካል ፡ ኢንትሮዳክሽን ፡ ቱ ፡ ሎው" ማለትም ፡ "የሕግ ፡ ታሪካዊ ፡ መግቢያ" በተባለው ፡ ኮርስ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤ ሀብትና ፡ መንግ ሥት ፡ ስላሉ ፡ አቋሞች ፡ አመጣጥ ፡ ሲሰጥ ፡ በዚሁ ፡ ኮርስ ፡ የክርስቲያንና ፡ የሮማው ያን ፡ ሕግ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ተፅእኖ ፡ እንደነበረው ፡ ይተነተን ፡ ነበር ። በሦስተኛው ፡ ኮርስ ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ አዲሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሁኔታና ፡ መሠረታዊ ፡ ሃሳቦች ፡ ለተማሪዎቹ ፡ ተሰጥቷል ።[50] በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ (፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡) "በመጀመሪያው ፡ ላይ ፡ የሮማውያንን ፡ ሕግ ፡ 'እንዳለ' አድ ርጎ ፡ ማስተማር ፡ በተለይም ፡ ለዘመናዊ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ስልቶችና ፡ ለሚመጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሆኑትን ፡ የሮማውያን ፡ አቋሞች ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ስለሚታሰብ"[51] ወደ ፡ ሮማውያንና ፡ ወደ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መግቢያ ፡ የሚሆን ፡ ኮርስ ፡ ተጣምሮ ፡ ይሰጥ ፡ ነበር ። ሌላው ፡ ኮርስ ፡ ደግሞ ፡ በአዲሱ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ስለሚገኙት ፡ ቅጣቶች ፡ ችግር ፡ በጥልቅ ፡ ይተ ንተን ፡ ነበር ። በመጨረሻም ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መታወጅ ፡ ስለሕገ ፡ መንግሥቱና ፡ ስለመንግሥቱ ፡ የሚሰጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ኮርስ ፡ እንዲኖር ፡ አስገደደ ።[52] በሦስተኛው ፡

48. ፻፳፭ ፡ አመልክተው ፡ ነበር ። እላይ ፡ ይመለከቷል ።
49. የምሩቃኖቹ ፡ ስም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነበር ። አበበ ፡ ጉዋንጉል ፤ አለማየሁ ፡ እሸቴ ፤ አሥራት ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፤ ፊቃደ ፡ ሥላሴ ፡ ዘውዴ ፤ ሀማዊ ፡ ጆርጅ ፤ ለገሠ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፤ ወርቁ ፡ ፈረደ ፤ ወርቁ ፡ ተፈራ ።
አስተማሪዎቹም ፡ በረከተ ፡ አብ ፡ ኃ/ሥላሴ ፤ ቺቺኖቪች ፡ (የሙሉ ፡ ጊዜ) ፡ እና ፡ ግራቨን ፡ ነበሩ ።
50. የ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዩ ፡ ኮ ፡ መጽሔት ፡ ገጽ ፡ ፻፸፪—፸፬ ።
51. እዚያው ፡ ገጽ ፡ ፩፻፸፬ ።
52. (እዚያው ፡ ገጽ ፡ ፻፶፩) ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ፵፱ ፡ በተጠቀሰው ፡ በመጀመሪያው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የሕግ ፡ መምህር ፡ በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ ተሰርቷል ።

ዓመት ፡ (፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የውሉ ፡ ክፍል ፡ በመጀመሪያ ፡ ስለወጣ ፡ በቀደምትነት ፡ ይኸው ፡ ክፍል ፡ እንዲሰጥ ፡ ተደረገ ።[53] በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ ስለተወሰኑ ፡ ዓይነት ፡ ወንጀል ፡ ስለሚናገረው፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ኮርስ ፡ ይሰጥ ፡ ነበር ።[54] በጠቅላላው ፡ የትምህርቱ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ በሰፊው ፡ የተሰጠበት ፡ ምክንያት ፡ ሕጉ ፡ በሙሉ ፡ ስለ ወጣ ፡ ነው ።

የመጨረሻው ፡ ፈተና ፡ በሰኔ ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲሆን ፡ ስምንት ፡ ተማሪዎች ፡ ባጥጋቢ ፡ ውጤት ፡ ተመርቀዋል ።[55] ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ት/ቤቱ ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአፈሴል ፡ ሥራውን ፡ አቋርጦ ፡ ተዘጋ ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ስለሕግ ፡ ትምህርት ፡ አሰጣጥ ፡ እቅድ ፡ የነበረባቸውን ፡ ኃላፊነት ፡ ይህ ፡ የአሁኑ ፡ ጸሐፊ ፡ እንዲረከባቸው ፡ ጠይቀው ፡ ነበር ። ት/ቤቱ ፡ የተዘጋው ፡ አዲስ ፡ የወጡትን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የንግድ ፡ ሕጎች ፡ (በግንቦት ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ደረጃ ፡[56] ሕጎቹን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊያውሏቸው ፡[57] የሚችሉ ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ማሰልጠንና ፡ በብዛት ፡ ማፍራት ፡ በሚገባበት ፡ ወቅት ፡ ስለነበር ፡ የትምህርቱ ፡ መቋረጥ ፡ በሀገሪቱ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ መስፋፋትና ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ለኅብረተ ፡ ሰቡና ፡ ለኢኮኖሚው ፡ ዕድገት ፡ እንቅፋት ፡ ሆኖአል ።

## ሠ/ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ "ጫፍ ፡ ጫፉን" ፡ በአርትስ ፡ ፋክልቲ ፡ ስለመሰጠቱ ፡ (፲፱፻፵፬–፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡)

በጠቅላላው ፡ ስንመለከት ፡ የወትሮው ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ የሚያስመሰግኑት ፡ ነገሮች ፡ አሉ ። በነበረው ፡ ትንሽ ፡ አቅም ፡ ዘመናዊ ፡ የሆነ ፡ ከሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ በኋላ ፡ የሚሰጥ ፡ ትምህርት ፡ አዘጋጅቶ ፡ ነበር ። ደግሞም ፡ ክፍ ፡ ወዳሉት ፡ ክፍሎች ፡ ያሉት ፡ ተማሪዎች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ትምህርት ፡ እንዲያጠኑ ፡ በማሰብ ፡ የሚሰጠውን ፡ የትምህርት ፡ ዓይነት ፡ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ አበዛ ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ የአርትስ ፡ ፋክልቲ ፡ ተማሪዎች ፡ ሊያማርጡና ፡ ሊወስዱ ፡ የሚችሉት ፡ ያስተዳደር ፡ የመምህራን ፡ ማሰልጠኛ ፡ ትምህርትና ፡ የኢኮኖሚክስ ፡ ትምህርት ፡ አጥጋቢ ፡ በሆነ ፡ ሁኔታ ፡ አበርክቷል ። እነዚህም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ትምህርቶች ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ እራሳቸውን ፡ የቻሉ ፡ ክፍሎች ፡ ወይም ፡ ቅርንጫፎች ፡ በኋላም ፡ ለምሳሌ ፡ እንደ ፡ መምህራን ፡ ማሰልጠኛው ፡ ትምህርት ፡ ክፍል ፡ እራሳቸውን ፡ የቻሉ ፡ ፋክልቲዎች ፡ ሆነዋል ።

በዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ጊዜ ፡ (ከ፲፱፻፵፬—፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡) የተጻፉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጽሔቶች ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቀን ፡ በአርትስ ፡ ፋክልቲ ፡ ወይም ፡ በማታው ፡

53. እዚያው ፡ ገጽ ፡ ፻፳፯

54. እዚያው ፡ ገጽ ፡ ፻፳፱

55. ጥቂቶቹ ፡ አሁን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደረጃ ፡ ደርሰዋል ፡ ለምሳሌ ፡ ወርቁ ፡ ተፈራ ፡ አሁን ፡ ኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ ሲኖራቸው ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲውም ፡ ባልደረባ ፡ ሆነዋል ። ሻለቃ ፡ አበበ ፡ ጉዋንጉል ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ አገኝተው ፡ የማታ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ በሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ መምህር ፡ ሆነዋል ። ሻለቃ ፡ ለገሠ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ደግሞ ፡ ኤል ፡ ኤል ፡ ኤም ፡ ሲኖራቸው ፡ በፖሊስ ፡ ኮሌጅና ፡ በሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ ያስተምራሉ ። ፈረደ ፡ ወርቁ ፡ ደግሞ ፡ ከፈረንሣይ ፡ አገር ፡ በሕግ ፡ የዶክተር ፡ ማዕረግ ፡ አግኝተዋል ፤ ወዘተ ።

56. የዲግሪ ፡ ኮርስ ፡ መስጠቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ነበረበት ፡ ፺ ፡ ቼቺኖቪች ፤ በ፳፰ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ይመለከታል ።

57. ያልተዋሀደና ፡ ርዝራዥ ፡ የሆነ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ለጥቂት ፡ የአርትስ ፡ ፋክልቲ ፡ ተማሪዎች ፡ ማስተማር ፡ እንዲህ ፡ ላለው ፡ ትምህርት ፡ ምትክ ፡ ሲሆን ፡ አይችልም ። ክታች ፡ ይመለከታል ።

ክፍል ፡ ለመስጠት ፡ ተገደጋግሞ ፡ መሞከሩን ፡ ያመለክታሉ ። ግን ፡ ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ "ለሕግ ፡ ዝግጅት" ተብሎ ፡ በሙሉ ፡ ልብ ፡ ሳይሆን ፡ በአጠራጣሪ ፡ ደረጃ ፡[58] ከተቋቋ መው ፡ ፕሮግራም ፡ በስተቀር ፡ ይህ፡ በአርትስ ፡ ፋክልቲ ፡ ሲሰጥ፡ የነበረው ፡ የሕግ ፡ ትም ህርት ፡ የተቀናበረ ፡ ፕሮግራም ፡ ኖሮት ፡ በሙያ ፡ ደረጃ ፡ አልተሰጠም ። እራሱን ፡ የቻለ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ካልተቋቋመ ፡ በስተቀር ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ በአጠቃላይ ፡ መልክ ፡ መቅረቡ ፡ ወይም ፡ ዝንባሌአቸው ፡ ወደሌላ ፡ ከሆኑ ፡ ትምህርቶች ፡ ጋር ፡ ተደባልቆ ፡ በአርትስ ፡ ፋክልቲ ፡ መሰጠቱ ፡ ወደፊት ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ ለማቋቋም ፡ መሠረት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡ ነበር ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጠው ፡ የአርትስን ፡ ትምህርት ፡ እንዲደግፍ ፡ ያህል ፡ ሆኖ ፡ ለምሳሌ ፡ ሲሰጥ ፡ የነበረው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ለኤኮኖ ሚክስ ፡ ወይም ፡ ለአስተዳደር ፡ ትምህርት ፡ የሚረዳ ፡ የገንዘብ ፡ ነክ ፡ ሕግ ፡ ነበር ።[59]

ሆኖም ፡ አንዳንድ ፡ የአርትስ ፡ ፋክልቲ ፡ ቅርንጫፎች ፡ በውጭ ፡ ሀገር ፡ የሕግ ፡ ዲግሪ ፡ ክርስ ፡ ለመውሰድ ፡ የሚያስችል ፡ በቂ ፡ መሠረታዊ ፡ ትምህርት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጊዜ ፡ ለተማሪዎቹ ፡ ይሠጡ ፡ ነበር ። ለምሳሌ ፡ የሀገሪቷ ፡ ሕግ ፡ ገና ፡ ባልወጣበትና ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲውም ፡ ገና ፡ ባልተቋቋመበት ፡ ጊዜ ፡ ጥቂቶቹን ፡ የአርትስ ፡ ባችለር ፡ ዲግሪ ፡ የነበራቸውን ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ የሕግ ፡ ባችለር ፡ ዲግሪ ፡ እንዲያገኙ ፡ አስችሏ ቸዋል ።[60]

## ረ/ የኮሌጁ ፡ ዘመን ፡ ፍጻሜና ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ በሙያ ፡ ደረጃ ፡ ለመስጠት ፡ ማንሠራራቱ ፡ (፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡)

የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ሙያን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ማደር ጀት ፡ የመጀመሪያው ፡ ዓላማው ፡ አድርጎ ፡ በታህሣሥ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተቋ ቋመ ። የፈተኛው ፡ የዩኒቨርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ከመዘጋቱ ፡ ከብዙ ፡ ወራት ፡ በፊት ፡ ስለ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ መቋቋም ፡ የነበረው ፡ ዓላማ ፡ ለአዲሱ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ቀርቦ ፡ ጸድቆ ፡ ነበር ።

አዲሱ ፡ ሁኔቱ ፡ ይህ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተንቆ ፡ ለነበረው ፡ ከዲግሪ ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ደረጃ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ማቋቋም ፡ ዓላማ ፡ ምቹ ፡ ሆነ ። ዩኒቨርሲቲው ፡ ያቋቋመው ፡ የሕግ ፡ ደርግ ፡[61] ፊት ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕግ ፡ ይማሩ ፡ እንደነበሩት ፡ ተመሳሳይ ፡ ሥራ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ከዲግሪ ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ደረጃ ፡ እንዲማሩ ፡ ወዲያውኑ ፡ ወሰነ ።[62] ይህንን ፡ ትምህርት ፡ ለማግኘት ፡ የሚፈልጉት፡ ሰዎች ፡ ቁጥር ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እየጨመረ ፡ ሄዶ ፡ ኖሮ ፡ ውሳኔው ፡ እንደተሰጠ ፡ ት/ቤቱ ፡ ፬፻፺ ፡ ተማሪዎች ፡ መቀበል፡ ችሏል ።

---

58. መሪው ፡ የራሱን ፡ ትምህርት ፡ ለመምረጥና ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ አልነበረውም ። ከ፲፱፻፶—፶፪ ተመርቀው ፡ ከነበሩት ፡ ተማሪዎች ፡ በቢ ፡ ኤ ፡ ዲግሪአቸው ፡ ላይ ፡ "ከሕግ ፡ በፊት" የሚል ፡ ቅጥያ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ የነበሩት ፡ ጥቂቶቹ ፡ ምሩቃን ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ። አብርሃም ፡ ገብሬ ፡ ማርያም ፤ አሰግድ ፡ ተሰማ ፤ በቀለ ፡ ናዲ ፤ ገብሬ ፡ መስቀል ፡ ቢያድግልኝ ፤ ተፈሪ ፡ ብርሃኔ ፤ ተሾገር ፡ ውቤ ፤ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዲንሣ ፡ ሌርሣ ፤ ሐጐስ ፡ ገብሬ ፡ የሱስ ፤ ሀማዊ ፡ ጆርጅ ፤ ከበደ ፡ ሐብቴ ፤ መላከ ፡ ሰላም ፡ በቀለ ፤ መኮብብ ፡ ገበየሁ ፤ ሳሙኤል ፡ አለማየሁ ፤ ተስፋዬ ፡ የማነ ።

59. ለሌላ ፡ ምሳሌ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የቺቺኖቪች ፡ ማስታወሻ ፡ ፭፮ ፡ ገጽ ፡ ፭፬ ፡ እና ፡ ማስታወሻ ፡ ፴ ፡ ይመለከቷል ።

60. በተለይ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ በኪውቤክ ፡ በሚገኘው ፡ ማጊል ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የወሰዱት ፡ ጥናት ፡ ነው ። (እላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ማስታወሻ ፡ ፳ ፡ ይመልከቷል ።)

61. የደርጉ ፡ አባሎች ፡ ከፍተኛ ፡ ሥራና ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ የሕግ ፡ ዲግሪ ፡ ያላቸው ፡ ፳ ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ ፫ ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ኤክስፐርቶች ፡ ነበሩ ።

62. እላይ ፡ ይመለከታል ።

ኮርሶቹ ፡ የተጀመሩት ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ሲሆን ፡ ከመጀመሪያው ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ክፍል ፡ ተለይተው ፡ ነበር ። ወደ ፡ እንግሊዝኛው ፡ ክፍል ፡ የሚገቡት ፡ የተሻለ ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ ስለነበራቸውና ፡ የእንግሊዝኛም ፡ ቋንቋ ፡ ከአማርኛው ፡ ይልቅ ፡ የሕግ ፡ ፈሊጥን ፡ የሚገልጹ ፡ ቃላት ፡ በበለጠ ፡ ስላለው ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ክፍል ፡ ደረጃ ፡ የላቀ ፡ ስለነበር ፡ ከእጩዎቹ ፡ የሚፈለገው ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ ከድሮው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነበር ። ሀገሪቷ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ እንደሚያስፈልጓት ፡ በመገንዘብ ፡ ኮሚቴው ፡ በቀለም ፡ ትምህርትና ፡ በቃል ፡ ጥያቄ ፡ ላይ ፡ ተመሥርቶ ፡ የነበረውን ፡ የመግቢያ ፡ ደረጃ ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ገብተው ፡ ሊያሳካላቸው ፡ ያልቻሉት ፡ ደግሞ ፡ ከሌሎቹ ፡ ጋር ፡ ተወዳድረው ፡ ሲወድቁ ፡ እንዲወጡ ፡ ተወሰና ፡ በዚሁ ፡ የማጣሪያ ፡ ዘዴ ፡ በመጀመሪያው ፡ ትምህርት ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፡ ፫፻ ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ ትምህርቱን ፡ ለመከታተል ፡ ቀሩ ።

ለሚሰጡት ፡ ትምህርቶች ፡ ሁሉ ፡ ሕጎች ፡ ወጥተው ፡ ስለነበር ፡ የማስተማሩ ፡ ጉዳይ ፡ በጣም ፡ ቀለለ ፤[63]

<u>የተሰጡት ፡ ኮርሶች ፤</u>

ሕገ ፡ መንግሥት ፤ በአማርኛውም ፡ በእንግሊዝኛውም ፡ ክፍል ፤ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፤ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ (ስለ ፡ ሰዎች፤ ስለቤተ ፡ ሰብ) ፤ (ስለውሎችና ፡ የንግድ ፡ ሕግ)[64] ነበሩ ።

እነዚህ ፡ ከዲግሪ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ማዕረግ ፡ የሚያስገኙ ፡ ኮርሶች ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ቋሚ ፡ የትምህርት ፡ ዓይነት ፡ ሲሆኑ ፡ በኋላም ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ ሲቋቋም ፡ ከት/ቤቱ ፕሮግራም ፡ ጋር ፡ ተዋህደዋል ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ደርጉ ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲን ፡ ለማቋቋም ፡ ዝግጅት ፡ ጀመረ ። የፋክልቲው ፡ መቋቋም ፡ ሁለት ፡ ችግሮች ፡ ነበሩት ። አንደኛ ፤ ከዩኒቨርሲቲው ፡ በጀትና ፡ ገንዘብ ፤ እንዲሁም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ መምህራን ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ማስመጣት ፡ አስፈለገ ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ቻንስለር ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ከፍተኛ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ የማጠናቀቁን ፡ ተግባር ፡ ወሰዱ ። ደርጉን ፡ የሚመለከት ፡ ሁለተኛው ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ ለሕግ ፡ ዲግሪ ፡ ትምህርት ፡ እጩዎችን ፡ ማግኘትና ፡ ለሀገሪቱ ፡ ጠቃሚ ፡ የሚሆነውን ፡ የትምህርት ፡ ዓይነት ፡ ማዘጋጀት ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ከፍተኛው ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ይህንን ፡ ጸሐፊ ፡ የሚጨምር ፡ ደርግ ፡ ተቋቁሞ ፤[65] ለመጀመሪያ ፡ ፳፯ ፡ ሰዎችን ፡ አነጋገር ። ይኸው ፡ ደርግ ፡ ት/ቤቱ ፡ ለመግባት ፡ ስለሚያስችለው ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፤ ስለሚሰጠው ፡ ዲግሪ ፤ ትምህርቱን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ መፍጀት ፡ እንዳለበት ፤ በተገኙት ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ ምርምር ፤ ከምክር ፡ ቤቱ ፡ ስለሚገኙ ፡ ሪኮርዶችና ፤[66]

---

63. በመጨረሻ ፡ የወጣው ፡ የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

64. አስተማሪዎቹም ፡ ቅደም ፡ ተከተላቸው ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በረከት ፡ አብ ፡ ሥላሴ ፤ ንርአዮ ፡ ኢሳኢያስ ፤ ፊሊፕ ፡ ግራቫን ፤ ቻርለስ ፡ ማቲው ፤ በላቸው ፡ አሥራት ፤ ተሾመ ፡ ገብረ ፡ ማርያምና ፡ መሐመድ ፡ አብዱራህማን ፡ ነበሩ ።

65. በማያዝያ ፡ ፩ ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ፡ም ፡ ተመርጠው ፡ የነበሩት ፡ የዝቅተኛው ፡ ደርግ ፡ አባሎች ፡ በላቸው ፡ አሥራት ፤ ጌታቸው ፡ ከብረት ፤ በረከት ፡ አብ ፡ ኃ/ሥላሴ ፤ ደብሊዮ ፡ ቡሁጂያር ፤ ፊሊፕ ፡ ግራቫንና ፡ ቹቹ ኖቪች ፡ ነበሩ ።

66. በዚህ ፡ መስመር ፡ መውጊድ ፡ የነበረባቸው ፡ የምርምሩ ፡ እንቅፋቶች ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ በቹቹኖቪች ፡ ፩፰ኛው ፡ ማስታወሻ ፡ ተገልጸዋል ። ጹሑፉም ፡ ከታች ፡ በተጠቀሰው ፡ በደርጉ ፡ ሪፖርት ፡ ተጠቃሏል ፡

ስለሚሰጠው ፡ ትምህርት ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲው ፡ አቅርቧል ። ይህ ፡ በ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኮሚቴው ፡ የጻፈው ፡ ሪፖርት ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ለተሾሙት ፡ ዲን ፡ ጄምስ ፡ ሲ ፡ ኤን ፡ ፖል ፡ ቀርቦ ፡ ከሥርዓተ ፡ ትምህርቱ ፡ በስተቀር ፡[67] ሌላው ፡ ሃሳብ ፡ በብዛት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ውሏል ።

በመስከረም ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲው ፡ በአጥጋቢ ፡ ሁኔታ ፡ ተጀመረ ። የፋክልቲውም ፡ ዕድገት ፡ በዲኑ ፡ ሪፖርት ፡ ተጽፎ ፡ በየጊዜው ፡ በሚወጣው ፡ በዚህ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ ታትሟል ።

67. ከአሜሪካ ፡ የመጡት ፡ አስተማሪዎች ፡ ሃሳብ ፡ አመዝኖ ፡ ፀና ።

## ተቀጥላ ።

ከዚህ ፡ በታች ፡ ከብዙ ፡ ሙከራ ፡ በኋላ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ልናረጋግጥና ፡ ልንመዘግብ ፡ የቻልነውን ፡ እ. ኤ. አ. የ፲፱፻፶፭ ዓ ፡ ም ፡ ና ፡ እ. ኤ. አ. የ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ምሩቃን ፡ ባሁኑ ፡ ወይም ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ የያዙትን ፡ ማዕርግ ፡ ሥልጣንና ፡ (ላይ ፡ በ፳፱ና ፡ በ፳፱ ፡ ተመልከት፡) ካለም ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ከተመረቁ ፡ በኋላ ፡ የጻፏቸውን ፡ ጽሑፎች ፡ እናቀርባለን ። ከስማቸው ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ቅንፍ ፡ ውስጥ ፡ ከዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ ተጨማሪ ፡ የያዙት ፡ ዲግሪና ፡ ማዕርግ ፡ ካለ ፡ ተጠቅሷል ። እ. ኤ. አ. የ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የከፍተኛ ፡ ዲፕሎማ ፡ ተመራቂዎች ፡ (ላይ ፡ በ፵፪) ለብቻቸው ፡ ሳይሆን ፡ እ. ኤ. አ. ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ. ም የመጀመሪያ ዲፕሎማ ፡ ምሩቃን ፡ ጋር ፡ ተጨምረው ፡ ተጠቅሰዋል። ይ ፡ በ፳፱) ፕሪ ፡ ሎው ፡ የቢ፤ኤ. ፡ ተመራቂዎች ፡ እዚህ ፡ ውስጥ ፡ አልተመዘገቡም ።

ሀ/ እ. ኤ. አ. የ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ ተመራቂዎች ።

| | | |
|---|---|---|
| ፩. | አበበ ፡ ተፈሪ ፡ (ብሪጋዴር ፡ ጀኔራል) ። | የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት፡አባል። |
| ፪. | አሸናፊ ፡ ቤተ ፡ ማርያም ። | በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ የክፍለ፡ ሀገር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ። |
| ፫. | አሰፋ ፡ ጸጋዬ ፡ (ቢ ፡ ኤ ፤ ኤል ፡ ኤል ፡ ቢ) ። | የኢትዮጵያ ፡ ንግድ ፡ ባንክ ፡ ሕግ ፡ አማካሪ ። |
| ፬. | አጥናፌ ፡ ፀሐይ ። | ጠበቃ ፤ ክፍል ፡ 'ሀ' ደረጃ ። |
| ፭. | በቀለ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ። (ኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፤ የተከበሩ) ። | አዲስ ፡ አበባ ፡ ጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዳንት። |
| ፮. | በየነ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ። | ማዕርግ ፡ አልታወቀም ። |
| ፯. | ዳዊት ፡ ገብሩ ፡ (ኰሎኔል) ። | የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር፡ቤት፡አባል። |
| ፰. | ደበበ ፡ ሁሪሴ ፡ (ኤም ፡ ሲ ፡ ኤል ፤ ሌተና ፡ ኰሎኔል) ። | በፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ሀላፊ ። |
| ፱. | ኢጌታ ፡ ፈይሳ ፡ ባልቻ ። | ማዕርግ ፡ አልታወቀም ። |
| ፲. | ኢያሱ ፡ ገብረ ፡ ሐዋርያት ፡ (ሻምበል ፤ የተከበሩ ) ። | ጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ። |
| ፲፩. | ፈቃደ ፡ ሥላሴ ፡ ጌታሁን ፡(ሻለቃ ፤ የተከበሩ) ። | ጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ። |
| ፲፪. | ገብሬ ፡ ወዳጆ ። | ትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ የትምህርት ፡ ይዞታ ፡ ጥናት ፡ ክፍል ። |
| ፲፫. | ኃይሉ ፡ ነጋው ። | የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ። |
| ፲፬. | ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ወልደ ፡ ኪዳን ፡ (ፊታውራሪ) ። | የየረርና ፡ ከረዩ ፡ አውራጃ ፡ ገዢ ። |
| ፲፭. | ሕይወት ፡ ጎዳሩ ፡ (ቀኛዝማች) ። | ጠበቃ ፡ ክፍል ፡ 'ሀ' ደረጃ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ፲፮. | ሆቫኖስ ፡ ካይፓጊያን ። | የአንበሳ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ኩባንያ ፡ ዋና ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ። |
| ፲፯. | ካሣ ፡ በየነ ፡ (ሌል ፡ ሌል ፡ ቢ ፤ የተከበሩ) ። | አሥመራ ፡ ጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዳንት ። |
| ፲፰. | ቀና ፡ ጉማ ፡ (ሻምበል) ። | የመሬት ፡ አሻሻጭ ። |
| ፲፱. | ከበደ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ (ቢ ፡ ኤ ፤ ሌል ፡ ሌል ፡ ቢ ፤ የተከበሩ) ። | ኮሚሺነር ፤ በሠራተኛ ፡ ማስተዳደሪያ ፡ መ/ቤት ፡ ምክትል ፡ ሚኒስትር ፤ በእንግሊዝኛ ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ፡ ደርሰዋል ። |
| ፳. | ኪዳኔ ፡ ማሾ ። | ጠበቃ ፤ ክፍል ፡ ‘ሀ’ ደረጃ ። |
| ፳፩. | ለገሠ ፡ ወልደ ፡ ሐና ፡ (ኰሎኔል ክቡር) ። | በኮንጎ ፡ ዲሞክራቲክ ፡ ሬፑብሊክ ፡ አምባሳደር ። |
| ፳፪. | ለማ ፡ ፈይሳ ። | የ‘ኤልሶለም’ ዋና ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ። |
| ፳፫. | መብራቱ ፡ ፍስሐ ፡ (ብሪጋዴየር ፡ ጄኔራል) ። | የዱር ፡ አራዊት ፡ ጥበቃ ፡ ክፍል ዋና ፡ አስተዳዳሪ ። |
| ፳፬. | መሐመድ ፡ በድሪ ። | በግል ፡ ሥራ ። |
| ፳፭. | ነጋሽ ፡ ደነቀ ። | ማዕርግ ፡ አልታወቀም ። |
| ፳፮. | ፓንዲ ፡ ቢ. ጄ. | የኢንሹራንስ ፡ ወኪል ። |
| ፳፯. | ስሜ ፡ ታከለ ። | የንብረት ፡ ማልሚያና ፡ ማስፋፊያ ፡ አክሲዮን ፡ ማኅበር ። |
| ፳፰. | ሸምሱ ፡ አህመድ ። | የቀ. ኃ. ሥ. በጎ አድራጎት ድርጅት፡ ምክትል ፡ አስተዳዳሪ ። |
| ፳፱. | ሺፈራው ፡ አማረ ፡ (ኰሎኔል) ። | በፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ የወንጀለኛ ፡ ምርመራ ፡ ክፍል ፡ ኃላፊ ። |
| ፴. | ስለሺ ፡ ድፋባቸው ፡ (ሌታውራሪ ፤ ኰሎኔል) ። | የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባል ። |
| ፴፩. | ታደሰ ፡ ድልነሳው ። | ጠበቃ ፡ ክፍል ፡ ‘ሀ’ ደረጃ ። (በዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ የከፍተኛ ፡ ትምህርታቸውን ፡ በማጠናቀቅ፡ላይ፡) |
| ፴፪. | ታደሰ ፡ መንገሻ ፡ (ክቡር ፡ አፈ ንጉሥ) ። | ከሥራ ፡ ተሰናብተዋል ፡ ቀድሞ ፡ የጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍርድ ፡ ቤት አ. አበባ ፡ ፕሬዚዳንት ። |
| ፴፫. | ተፈራ ፡ ደግፌ ፡ (ቢ.ኮም.) ። | የኢትዮጵያ ፡ ንግድ ፡ ባንክ ፡ ጠቅላይ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፤ ‘ካፒታል ፎርሜሽን ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፡’ የተባለ ፡ መጽሐፍና ፡ (አ. አበባ ፤ ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፤ ፲፱፻፶፰ ዓ.ም.) ብዙ ጽሁፎች ፡ ደርሰዋል ። |
| ፴፬. | ጥበቡ ፡ በየነ ፡ (የተከበሩ) ። | የአ. አበባ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ (ቀድሞ ፡ የጠቅላይ ፡ ን. ነ. ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዳንት ። |

| | | |
|---|---|---|
| ፴፭. | ተፈሪ ፡ ለማ ፡ (ክቡር ፡) | በንግድ ፡ ኢንዱስትሪና ፡ ቱሪዝም ፡ ሚኒስቴር ፡ ምክትል ፡ ሚኒስትር ። |
| ፴፮. | ጥላሁን ፡ ብሩ ። | በሥራ ፡ ሚኒስቴር ፡ ዲሬክተር ፡ |
| ፴፯. | ወርቁ ፡ በሻዬ ፡ (ሊሴንስ ፡ እን ፡ ድሮ) | አርፈዋል ። |
| ፴፰. | ዘውዴ ፡ መሸሻ ፡(ሊሴንስ ፡ እን ፡ ድሮ፣) | በአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የሕግ ክፍል ፡ ሀላፊ ። |
| ፴፱. | ዘነበ ፡ ወርቅ ፡ ኃይሌ ፡ (ሌተና ፡ ኰሎኔል ) | አርፈዋል ። |

## ሰ. የ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ.ም. የሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ ተመራቂዎች ።

| | | |
|---|---|---|
| ፩. | አበበ ፡ ጓንጉል ፡ (ኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፣ ሻለቃ) ፤ | በፐብሊክ ፡ አድሚኒስትሬሽንና ፡ ጡረታ ፡ ኮሚሽን ፡ ሕግ ፡ አማካሪና፡ ምክትል ፡ ኮሚሽነር ፤ በቀዳማዊ ፡ ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ ክፍል ፡ አስተማሪ ። |
| ፪. | ዓለማየሁ ፡ እሸቴ ፡ (ሊሴንስ ፡ ድሮ) ፤ | ጠበቃ ፡ ክፍል ፡ 'ሀ' ደረጃ ። |
| ፫. | አሥራት ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፤ | ማዕረግ ፡ አልታወቀም ። |
| ፬. | ፈቃደ ፡ ሥላሴ ፡ ዘውዴ ፤ | በቀዳማዊ ፡ ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ ዋና ፡ ተቆጣጣሪ ። |
| ፭. | ሐማዊ ፡ ጆርጅ ፡ (ቢ.ኤ. ፤ ቢሲኤል) ፡ | ጠበቃ ፡ ክፍል ፡ 'ሀ' ደረጃ ። |
| ፮. | ለገሠ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ (ኤም. ሲ. ኤል. ፤ ሻለቃ) ፤ | በአባ ፡ ዲና ፡ ፖሊስ ፡ ኮሌጅ ፡ ሕግ ፡ አስተማሪ ፤ በቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ ሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ የማታ፡ ትምህርት ፡ ክፍል ፡ አስተማሪ ። |
| ፯. | ወርቁ ፡ ፈረደ ፡(ዶክተር ፡ እን ፡ ድሮ) ፤ | የኢትዮጵያ ፡ ብሔራዊ ፡ ባንክ ፡ ሕግ ፡ አማካሪ ። ሕግ ፡ ነክ ፡ የሆነ፡ በፈረንሳይኛ ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ደርሰዋል ። |
| ፰. | ወርቁ ፡ ተፈራ ፡ (ኤል. ኤል. ቢ.) ፤ | በቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ ሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ መምህር ፤ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ለከፍተኛ ትምህርት፡ በዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ይገኛሉ ። |